የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ጥር ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25[th] Year No 9
ADDIS ABABA 30[th], January 2019

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፴፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፡ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ...ገፅ ፲ሺ፮፻፹፰

CONTENT

Regulation No. 437 /2018

Definition of Powers, Duties and Organization of the Customs Commission Regulation........................................page 10688

ደንብ ቁጥር ፬፻፴፯/፪ሺ፲፩

<u>የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፡ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

በፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የጉምሩክ ኮሚሽን በህግ የተቋቋመ በመሆኑ፣

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በህግ በመደንገጉ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፩ (፪) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፣ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

REGULATION No. 437/2018

<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE THE DEFINITION OF POWERS, DUTIES AND ORGANIZATION OF THE CUSTOMES COMISSION</u>

**WHEREAS**, the Customs Commission is already established by law following the organizational and structural changes in the Federal Government Executive Organs;

**WHEREAS**, the Powers and Duties of the Commission are provided to be defined by the Council of Minister's Regulation;

**NOW THEREFORE,** the Council of Ministers has issued the following Regulation in accordance with Article 31 (2) of Proclamation No. 1097/2018 defining powers and duties of the Federal Executive Organs.

1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as "Definition of Powers, Duties and Organization of the Customs Commission Regulation No. 437/2018."

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፪/ "ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የጉምሩክ ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፡፡

፫/ በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴት ጾታም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፫. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችና የጉምሩክ ጣቢያዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## ፬. ዓላማ

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣

፪/ ወደ አገር በሚገቡና ወደ ውጭ አገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣

፫/ አግባብነት ያላቸውን የጉምሩክ ህጎችና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውንና ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

፬/ ወደ አገር እንዳይገቡና ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ወይም ስለአገባባቸውና ስለአወጣጣቸው ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች መቆጣጠር፣

፭/ የጉምሩክ ማጭበርበርን እና ኮንትሮባንድን መከላከልና መቆጣጠር፡፡

## 2. Definition

Unless the Context requires otherwise, in this Regulation:

1/ "Ministry or Minister" means the Ministry or Minister of Revenues, respectively.

2/ "Commission or Commissioner" means the Customs Commission or Commissioner, respectively.

3/ Any expression in the Masculine Gender will be applicable to the Feminine.

## 3. Head Office

The Commission shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices and customs stations elsewhere in Ethiopia or abroad as may be necessary.

## 4. Objectives

The Commission shall have the following objectives:

1/ To provide equitable, expeditious and quality service by establishing a modern customs administration system;

2/ To collect duties and taxes timely and efficiently on goods imported or exported;

3/ To implement relevant customs laws and international agreements approved and ratified by Ethiopia;

4/ To Control the import and export of prohibited or restricted goods;

5/ To prevent and control customs fraud and contraband.

## ፭. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፣ በህግ መሰረት ቀረጥና ታክስ እንዲሁም የፈቃድ እና የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣

፪/ የጉምሩክ ህጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የአስመጪዎች፣ የላኪዎች ወይም በማንኛውም ሰው ይዞታ ስር የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፣

፫/ በጉምሩክ ወደቦች፣ በወሰን አካባቢዎች እና በመተላለፊያ መንገዶች የጉምሩክ መቅረጫና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ አጥንቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያቋቁማል፣

፬/ የጉምሩክ መጋዘን ያቋቁማል፣ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች የሚከማቹበትን ሥፍራ ይወስናል፣ ዕቃዎች በአግባቡ መያዛቸውን ይቆጣጠራል፣

፭/ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ በዚህ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፮/ በጉምሩክ ወደቦችና በወሰን አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ ጣቢያዎች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይፈትሻል፣ የጉምሩክ ስነስርዓት ተፈጸሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣

፯/ ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር እንዳይላኩ በሕግ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸውን ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመባቸውን ዕቃዎች ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

## 5. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following powers and duties:

1/ To assess duty paying values, collect duties and taxes, collect license and service charges in accordance with laws;

2/ To inspect and examine documents of importers, exporters or any other person, for the purpose of enforcing customs laws;

3/ To carry out studies for the establishment of customs stations in any customs ports, frontier posts and transit routes, and implement same up on approval by the Ministry;

4/ To establish customs warehouses and approve the place for the deposit of import and export goods, establish warehouses, give license for those who establish customs warehouse, supervise the proper handling of deposited goods;

5/ To prevent and control the import or export of contraband goods and seize, take any legal actions on such goods and means of transportation of such goods;

6/ To inspect and search any goods and means of transport entered in to or departing from Ethiopia through customs ports, frontier posts and other customs stations, assure that they are being accustomed;

7/ To seize goods which are prohibited by the law not to be imported or exported , restricted or un accustomed goods and take the necessary legal measures;

፰/ ገቢና ወጪ ዕቃዎችን በተመለከተ መረጃዎችን ይይዛል፣ ያደራጃል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፣

፱/ ስለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አጣጣል፣ አተማመንና አሰባሰብ እንዲሁም ስለኮንትሮባንድ መከላከልና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት አጥንቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲/ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ባለቤት የሌላቸው፣ የተተዉ ወይም የተወረሱ ዕቃዎችን ያስተዳድራል፣ ይሸጣል፣ ያስወግዳል፣

፲፩/ በጉምሩክ ህጎች መሰረት ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፣

፲፪/ ለጉምሩክ ሥራ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችንና የተለያዩ ጽሁፎችን ያዘጋጃል፣

፲፫/ የቀረጥና ታክስ ስሌቶችን፣ አሰባሰብ፣ ሒሳብ አያያዝና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ዘመናዊ የአሠራር ዘዴዎችንና ሥርዓቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፬/ ብቃት ያላቸው የጉምሩክ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣

፲፭/ በመስኩ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፣ የቀረጥ ነፃ መብቶችንና ማበረታቻዎችን አጠቃቀም በመከታተልና በመቆጣጠር ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

፲፮/ የጉምሩክ ወንጀሎችን በሚመለከት የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣

8/ To collect, organize and disseminate data of imported and exported goods;

9/ To carry out studies for efficient system of levying, valuation and collection of customs duties and taxes as well as ways and systems of combating and repression of contraband activities, and implement the same up on approval;

10/ To sale, dispose, administer goods without owner, abandoned or forfeited;

11/ To issue, renew, suspend or cancel various types of licenses in accordance with the customs laws;

12/ To prepare forms and brochures necessary for customs activity;

13/ To apply and implement modern systems and methods for valuation, assessment and collection of taxes and duties and financial accounting and other related activities;

14/ To provide trainings to employees that enables the commission to obtain efficient, customs professional expertise;

15/ To provide efficient, equitable and quality service with in the sector based on the principles of transparency and accountability, and enforce the proper implementation of incentives and tax exemption granted to investors and ensure that the privileges are used for their intended purposes;

16/ To organize and compile statistical data on customs criminal offences and disseminate the information to others as may be necessary;

፲፯/ የጉምሩክ ህግን ለማስከበር የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፰/ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የጉምሩክ ሕግ በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል በፌደራል ፖሊስ የሚደራጀው እና የሚመደበው የፖሊስ ኃይል ስምሪትን በሚመለከት ከፌደራል ፖሊስ ጋር በጋራ ያቅዳል፣ ይፈጽማል፣ ይገመግማል፣

፲፱/ የጉምሩክ ላቦራቶሪ ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣

፳/ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አመራር መሠረት የጉምሩክ አስተዳደርን በሚመለከት ዓለምአቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣

፳፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላል፣

፳፪/ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ፮. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ፣

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነሮች፣እና

፪/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፯. የኮሚሽነሩ ተግባርና ኃላፊነት

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣

17/ To plan and implement awareness programs that will ease the enforcement of customs law;

18/ Plan, implement, evaluate in collaboration with Federal Police concerning the deployment of the police force organized pursuant to article 9 of this Regulation and other relevant laws to prevent criminal offences in violation of customs laws.

19/ To organize and operate customs laboratory;

20/ To make international agreements regarding the customs administration with the direction of the Ministry;

21/ To own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

22/ Perform such other related activities required for the attainment of its objectives.

## 6. Organization of the Commission

The Commission shall have:

1/ A Commissioner and Deputy Commissioners to be appointed by the prime Minister; and

2/ Necessary employees.

## 7. Powers and Responsibilities of the Commissioner

1/ The Commissioner shall be the Chief Executive Officer of the Commission and shall direct and administer the activities of the Commission.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Commissioner shall:

a) Exercise the Powers and Duties of the Commission specified under Article 5 of this Regulation;

ለ) የኮሚሽኑን ሠራተኞች በደንብ ቁጥር ፩፻፶፭/፪ሺ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ይውላል፣

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ) የፍትሐብሔር ክርክሮችን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ሊጨርስ ይችላል፣

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፣

ሰ) ስለ ሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የኮሚሽኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፰. <u>የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ኮሚሽነሮች፡-

፩/ የየስራ ዘርፋቸውን ተግባሮች በማቀድ፣በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳሉ፡፡

፪/ በኮሚሽነሩ የሚሰጧቸውን ሌሎች ስራዎች ያከናውናሉ፡፡

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ የተወከለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

b) Employ, administer, dismiss employees in accordance with Regulation No. 155/2008;

c) Prepare and submit to the Minister the annual plan and budget of the Commission and implement the same upon approval;

d) Effect payment in accordance with the approved budget and work program of the Commission;

e) May settle Civil disputes out of court in accordance with the directives issued by the Minister;

f) Represent the Commission in all its dealings with third parties;

g) Submit periodical reports to the Minister.

3/ The Commissioner may delegate part of his Powers and Duties to officials and employees of the Commission to the extent necessary for the management of the Commission's activities.

8. <u>Powers and Duties of the Deputy Commissioners</u>

The Deputy Commissioners shall:

1/ Support the Commissioner in planning organizing, directing and coordinating the activities of their respective sectors.

2/ Perform other activities directed to them by the Commissioner.

3/ In the absence of the Commissioner, the Deputy Commissioner specifically delegated by the Commissioner shall carry out the activities of the Commissioner.

**፱. የጉምሩክ ፖሊስ ስለማደራጀትና ስለመመደብ**

የፌደራል ፖሊስ ጉምሩክ ሕጎችን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ያሰለጥናል፣ለኮሚሽኑ ይመድባል፡፡

**፲. በጀት**

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

**፲፩. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**፲፪. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ሚንስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ደንብና መመሪያ በደንቡ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**፲፬. ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ኅዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር



**9. Organizing and Deploying Of Customs Police**

Federal Police shall have the responsibility to organize, train and deploy Customs Police force to prevent criminal offences in violation of customs law.

**10. Budget**

The Government shall allocate budget of the Commission.

**11. Books of Account**

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of account.

2/ The books of account and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Auditor General or by other Auditors designated by the Auditor General.

**12. Power to issue Directive**

The Ministry may issue Directives necessary for the effective implementation of this Regulation.

**13. Inapplicable laws**

Any Regulation or Directive that is inconsistent with this Regulation shall have no effect on matters covered by this Regulation.

**14. Effective Date**

This Regulation shall come in to force as of the 1st day of December 2018 of its approval by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa, this 30th Day of January, 2019.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**